በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የቅዱሳን አማላጅነት - ሁለተኛ ሳምንት

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## መጋቢት ፩ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

# አማላጅነት

- እግዚአብሔር ምልጃን የፈቀደው ለሰው ጥቅም ነው።
- ምልጃውም በሰማይና በምድር ላሉት እንደ ድልድይ ነው።
- በቅዱሳኑ ነፍሳት ፍቅርና ሥራ ካመንን ሰማያዊው ሥፍራ ከዚህ በኋላ የማይታወቅና የሚያስፈራ አይደለም።
- ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈልን የምድሩ ዜና ለሰማያውያኑ መላዕክትም ሆነ ላረፉት ቅዱሳን ነፍሳት ይደርሳል። እነርሱ ማን ንስሐ እንደ ገባ፣ ማን ንስሐ እንደሚያስፈልገው ያውቃሉ። ንስሐ በገባውም ኃጥእ ደስ ይላቸዋል። *ሉቃ 15፡7።*
- ታዲያ የምድሩን ዜና ካላወቁ እንዴት ሊደሰቱ ይችላሉ? ዛሬ በዚሁ ሰዓት በአንዱ የዓለም ክፍል ያለውን ዜና ካለንበት ሆነን ለማመን በሚያስቸግር ደረጃ ማየት የምንችልበት ዘዴ መፈጠሩን አይተን ከተቀበልን እግዚአብሔር አውቀው ደስ ይላቸዋል ያለውን ለመቀበል እንቸገር ይሆን?
- ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጸሎታችንን ያውቁታል ቅድመ እግዚአብሔርም ያሳርጉልናል። *በራዕ 5፡8* የተጻፈው የሚያስረዳን ይህን ነው። "መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና *ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ* ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።"
- ጌታችንም *በማቴ 18፡10* "ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ *መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ* እላችኋለሁና።" ያለን ይህንኑ የአማላጅነት ትምህርት የሚያጠናክር ነው።

# <u>የአማላጅነት ትምህርት - ያረፉ ቅዱሳን ያለውን ያውቃሉ</u>

- በራዕየ ዮሐንስ ስለ ሰማዕታት ነፍሳት የተገለጠውም ሌላው ትምህርት ነው፡፡ “አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ:: በታላቅ ድምፅም እየጮኹ:: ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ:: ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቊጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው::” *<u>ራዕ 6፡9-11፡፡</u>*

- ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ ስለፈሰሰው ደማቸው ጌታችንና አምላካችን እንዳልፈረደላቸው ያውቃሉ፡፡ ወደ እግዚአብሔርም በታላቅ ድምፅ እየጮኹ “ክፋት በምድር ላይ እንድሰለጥን እስከመቼ ትፈቅዳለህ? በሥጋ የበረቱት ልጆችህን ይበድሉአቸው ዘንድስ እስከመቼ ትፈቅዳለህ? ይህንንስ ደማቸውን እስከመቼ ያፈሳሉ?” በማለት ጠይቀዋል፡፡

- ታዲያ ሰማዕታቱ ይኽን እንዴት አወቁ? ያውቃሉ፡፡ በሃይማኖት ሕይወት የሚመስሏቸው ቅዱሳን ሲያልቁ ያውቃሉ፡፡ ሰማያዊው ዕውቀት ከምድራዊው የላቀ ነውና፡፡ “እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን::” እንዳለ፡፡ *<u>ካል ቆሮ 3፡18፡፡</u>*

-

# *<u>የቅዱሳን ዕውቀታቸው፣ ክብራቸውና አገልግሎታቸው</u>*

1. በምድር በኖረበት ዘመኑ ነቢዩ ሳሙኤል ስለጠፋች አህያ ተጠይቆ ነበር፡፡ ስለርሱም “ስሙ ቂስ የተባለ አንድ ብንያማዊ ሰው ነበረ እርሱም የአቢኤል ልጅ፥ የጽሮር ልጅ፥ የብኮራት ልጅ፥ የብንያማዊው የአፌቅ ልጅ፥ ጽኑዕ ኃያል ሰው ነበረ፡፡ ለእርሱም ሳኦል የሚባል የተመረጠ መልካም ልጅ ነበረው ከእስራኤልም ልጆች ከእርሱ ይልቅ መልካም የሆነ ሰው አልነበረም ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ፡፡ የሳኦልም አባት የቂስ አህዮች ጠፍተው ነበር ቂስም ልጁን ሳኦልን፦ ከብላቴኖቹ አንዱን ወስደህ ተነሣ፥ አህዮችንም ለመሻት ሂድ አለው፡፡ … እርሱም፦ *<u>እነሆ፥ አንድ የእግዚአብሔር ሰው በዚህች ከተማ አለ እርሱም የተከበረ ሰው ነው፥ የሚናገረውም ሁሉ በእውነት ይፈጸማል አሁን ወደዚያ እንሂድ ምናልባት የምንሄድበትን መንገድ ይነግረናል</u>* አለው፡፡…” ተብሏል፡፡ *<u>ቀዳ ሳሙ 9፡1-27፡፡</u>*

2. ነቢዩ ኤልሳዕ በምድር ሳለ ደቀ መዝሙሩ ግያዝ በድብቅ ሄዶ ከሶርያዊው ከንዕማን ስጦታን እንደተቀበለ አውቆ ነበር፡፡ “… እርሱ ግን ገብቶ በጌታው ፊት ቆመ ኤልሳዕም፡፡ ግያዝ ሆይ፥ ከወዴት መጣህ? አለው፡፡ እርሱም፦ እኔ ባሪያህ ወዴትም አልሄድሁም አለ፡፡ እርሱም፦ ያ ሰው ከሰረገላው ወርዶ ሊቀበልህ በተመለሰ ጊዜ ልቤ ከአንተ ጋር አልሄደምን? ብሩንና ልብሱን፥ የወይራውንና የወይኑን ቦታ፥ በጎችንና በሬዎችን፥ ወንዶችንና ሴቶችን ባሪያዎች ትቀበል ዘንድ ይህ ጊዜው ነውን? እንግዲህስ የንዕማን ለምጽ በአንተ ላይ፥ ለዘላለምም በዘርህ ላይ ይጣበቃል አለው፡፡ እንደ በረዶም ለምጻም ሆኖ ከእርሱ ዘንድ ወጣ፡፡” *<u>ካል ነገ 5፡25-27፡፡</u>*

3. የሶርያው ንጉሥ አገልጋይ ለንጉሡ ስለ ኤልሳዕ “ከባሪያዎቹም አንዱ፡፡ ጌታዬ ሆይ፥ እንዲህ እኮ አይደለም ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ፡፡” *<u>ካል ነገ 6፡11-2፡፡</u>*

4. ኤልሳዕ የእስራኤል ንጉሥ ይገድለው ዘንድ መልዕክተኛውን እንደላከበትና የመጣበትን የመከራ ሰዓት አስቀድሞ አውቆ ነበር፡፡ “ኤልሳዕ ግን በቤቱ ተቀምጦ ነበር፥ ሽማግሌዎችም ከእርሱ ጋር ተቀምጠው ነበር ንጉሡ ሰው ላካ መልእክተኛውም ገና ሳይደርስ ለሽማግሌዎች፡፡ ይህ የነፍሰ ገዳይ ልጅ ራሴን ይቈርጥ ዘንድ እንደ ላከ እዩ መልእከተኛውም በመጣ ጊዜ ደጁን ዘግታችሁ ከልክሉት የጌታው የእግሩ ኮቴ በኋላው ነው አላቸው፡፡ *<u>ሲናገራቸውም መልእክተኛው ወደ እርሱ ደረሰ</u>* እርሱም፦ እነሆ፥ ይህ ክፉ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፥ እግዚአብሔርን ገና እጠብቅ ዘንድ ምንድር ነኝ? አለ፡፡” *<u>ካል ነገ 6፡32-33፡፡</u>* ኤልሳዕ በሥጋ ሆኖ ድብቅ የሆኑትን ወይም ምስጢራትን የማወቅ ስጦታ ተሰጥቶት ነበር፡፡ታዲያ ደካማ ሥጋው ከተወገደለት በኋላ ምን ያህል የበለጠ ያውቅ ይሆን?

# *የቅዱሳን ዕውቀታቸው፣ ክብራቸውና አገልግሎታቸው*

5. ቅዱስ ጴጥሮስም ሐናንያና ሰጲራ በምስጢር ያደረጉትን አውቆ ገልጾላቸው ቀጥቷቸዋል፡፡ "ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው፡፡ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም፤ በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ፡፡ ጕበዞችም ተነሥተው ከፈኑት አውጥተውም ቀበሩት፡፡ከሦስት ሰዓት ያህል በኋላም ሚስቱ የሆነውን ሳታውቅ ገባች፡፡ ጴጥሮስም መልሶ፦ እስቲ ንገሪኝ፥ መሬታችሁን ይህን ለሚያህል ሸጣችሁትን? አላት፡፡ እርስዋም፦ አዎን፥ ይህን ለሚያህል ነው አለች፡፡ ጴጥሮስም፦ የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ስለ ምን ተስማማችሁ? እነሆ፥ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው አንቺንም ያወጡሻል አላት፡፡..." ተብሏል፡፡ *ሥራ 5:1-9፡፡*

6. ቅዱስ ጳውሎስም "... ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ፡፡" ብሏል፡፡ *ሥራ 20:29፡፡*

- ሐዋርያቱ በሥጋ በምድር ሳሉ ይኸን ያህል ከገለጠላቸው በሰማይ ታዲያ ምን ያህል አብዝቶ ይገልጥላቸው ይሆን?

- ቅዱሳን አውቀው ለሕዝቡ የሚገልጡት መልዕክት አላቸው፡፡ አሁን ከእኛ ጋር እንደኛ ሆነው በምድር ካሉትና ከዚህ ዓለም ካልተለዩት ይልቅ ይኸን ዓለም አሸንፈው በሰማይ የሚገኙትን እንጠይቃለን፡፡ "ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉና፡፡" *ዳን 12:3፡፡*

- "የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል፡፡" *ምሳሌ 4:18፡፡*
- "ሁልጊዜ ለጻድቃን ብርሃን ነው ፡፡" *ምሳሌ 13:9፡፡*
- "ኃጢአተኞች በደጎች ፊት ይጐነበሳሉ፥ ኀጥኣንም በጻድቃን በር፡፡፡፡" *ምሳሌ 14:19፡፡*
- "በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፡፡" *ዕብ 12:23፡፡*
- "የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና፥ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፥ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው፡፡" *ቀዳ ጴጥ 3:12፡፡*

# ቅዱሳንን ክብር የሚገልጡ ተጨማሪ ምሳሌዎች

1. የነቢዩ የኤልሳዕ አጥንት ታላቅ ተአምራትን ማድረግ ችሎ ነበር። ሳይጸልዩም የሞተውን ሰው በኤልሳዕ መቃብር ቢያደርጉት ዳግመኛ ሕይወት አገኘ። ያዳነው ሕይወት የሌለበት አጥንት ነበር። “ሰዎችም አንድ ሰው ሲቀብሩ አደጋ ጣዮችን አዩ፥ ሬሳውንም በኤልሳዕ መቃብር ጣሉት የኤልሳዕንም አጥንት በነካ ጊዜ ሰውዮው ድኖ በእግሩ ቆመ።” *ካል ነገ 13:21።* ታዲያ በሰማይ ያለች የኤልሳዕ ነፍሱ ምን ያህል የበለጠ ታደርግ ይሆን? በእርግጥም ነፍሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ከአጥንቱ ይልቅ ብርቱና አዋቂ ናት። ኤልሳዕን የሚመስሉ ቅዱሳን ነፍሳትስ ምንያህል የበለጠ መልካም ያደርጉልን ይሆን?
2. የቅዱስ ጳውሎስ የአካሉ ልብስ ወይም ጨርቅ ሕሙማንን በነካቸው ጊዜ ከሕመማቸው ይፈወሱና አጋንንትም ይወጡ ነበር። “አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፥ 19 2 አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው። እርሱም፦ አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት። 19 3 እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው። እርሱም፦ በዮሐንስ ጥምቀት አሉት። 19 4 ጳውሎስም፦ ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው። 19 5 ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤ 19 6 ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ። 19 7 ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር። 19 8 ወደ ምኵራብም ገብቶ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር። 19 9 አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ፥ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፥ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር። 19 10 በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ። 19 11 እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፥ 19 12 ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር።” *ሥራ 19:1-12።* ቅዱስ ጳውሎስን የሚመስሉ ቅዱሳን ነፍሳትስ ምን ያህል የበለጠ ነገርን በሰማይ ያደርጉ ይሆን?

# *በሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን አሁንም አሉ*

- ጌታችንም “ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን። እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም።” ብሎ ይህን እውነት አስተምሮናል። ስለዚህ እነዚያ ቅዱሳን ዛሬም አሉ። ታዲያ እንደሌሉ በመቁጠር እንዲጸልዩልን መጠየቅን ስለምን እንተዋለን? *ማቴ 22:31-32።*
- ሙሴና ኤልያስም ከጌታችን ጋር መታየታቸውን አንዘነጋውም። ሙሴ ከጌታችን መወለድ 1400 ዓመት አስቀድሞ አረፈ። ነገር ግን ከኤልያስ ጋር ወደ ሰማይ ተወስዶ ዛሬም በሕይወት ይኖራል። ነፍሳቸው አትሞትም!!! ከእኛ ኘኘልቅ ያያሉ ይሰማሉም። *ማቴ 17:4።*

# የቅዱሳን መላዕክት አማላጅነት

1. ***ስለ ኢያሩሳሌም-*** “የእግዚአብሔርም መልአክ መልሶ፦ አቤቱ፥ የሠራዊት ጌታ ሆይ፥ እነዚህ ሰባ ዓመት
የተቈጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? አለ። 1 13
እግዚአብሔርም መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው። 1
14 ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ። ስበክ እንዲህም በል። የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ በታላቅ ቅንዓት በኢየሩሳሌምና በጽዮን ቀንቻለሁ። 1 15 እኔ ጥቂት ብቻ
ተቈጥቼ ሳለሁ እነርሱ ክፋትን ስላገዙት፥ ባልተቸገሩት አሕዛብ ላይ እጅግ ተቈጥቻለሁ። 1 16 ስለዚህ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወደ ኢየሩሳሌም በምሕረት ተመልሻለሁ ቤቴ ይሠራባታል በኢየሩሳሌምም
ላይ ገመድ ይዘረጋበታል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦ 1 17 ደግሞም እንዲህ ስትል ስበክ።
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ከተሞቼ ደግሞ በበጎ ነገር ይረካሉ እግዚአብሔርም ደግሞ
ጽዮንን ያጽናናል፥ ኢየሩሳሌምንም ደግሞ ይመርጣል። 1 18 ዓይኖቼንም አንሥቼ እነሆ፥ አራት ቀንዶች
አየሁ። 1 19 ከእኔም ጋር ይነጋገር የነበረውን መልአክ። እነዚህ ምንድር ናቸው? አልሁት። እርሱም፦
እነዚህ ይሁዳንና እስራኤልን ኢየሩሳሌምንም የበተኑ ቀንዶች ናቸው ብሎ መለሰልኝ። 1 20
እግዚአብሔርም አራት ጠራቢዎች አሳየኝ። 1 21 እኔም። እነዚህ የመጡት ምን ሊሠሩ ነው? አልሁ።
እርሱም፦ አንድ ሰው ራሱን እስከማያነሣ ድረስ እነዚህ ቀንዶች ይሁዳን የበተኑ ናቸው እነዚህ ግን
ሊያስፈራሩአቸው፥ የይሁዳንም አገር ይበትኑ ዘንድ ቀንዳቸውን ያነሡትን የአሕዛብን ቀንዶች ሊጥሉ
መጥተዋል ብሎ ተናገረ። ” ***ዘካ 1፡12፦21፡***
2. ***ስለ ታላቁ ካህን ስለ ኢያሱ፦-*** “እርሱም ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ፥ ሰይጣንም ይከስሰው ዘንድ በስተ ቀኙ ቆሞ ነበር። እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ ሰይጣን ሆይ፥ እግዚአብሔር ይገሥጽህ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገሥጽህ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን? አለው።” ***ዘካ 3፡1-2።***
3. ***ያዕቆን እንደጠበቀውና እንዳዳነው፦-*** ያዕቆብ ኤፍሬምና ምናሴን በባረካቸው ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሯል። “ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፥ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅም ስም በእነርሱ ይጠራ በምድርም መካከል ይብዙ።” ***ዘፍጥ 48፡16።***
4. ***ቅዱስ መጽሐፍ ስለ መላዕክት የተናገረውንም መርሳት የለብንም።*** “ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?” ***ዕብ 1፡14።***

# ቅዱሳን በጌታችን ዘንድ የተሰጣቸው ክብር!

1. ለሰው ልጆች በጎነትን ፣ ምሕረትን ይለምኑ ዘንድ  እግዚአብሔር በሰጣቸው አማላጅነታቸው  ያማልዱን ዘንድ እንጠይቃለን። እርሱ እግዚአብሔር ታላቅ ክብርን ሰጥቶ ወዶአቸዋልና።

2. እግዚአብሔር ስሙን ከስማቸው ጋር እያደረገ ይናገር ነበር። "ደግሞም፦ እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው።" *ዘጸ 3፡6።*

3. ስማቸው ሲጠራ ቃልኪዳኑን እያሰበ ስለሚራራ ሙሴ አንስቶ ለምኖባቸዋል። "ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፥ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፥ ለዘላለምም ይወርሱአታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ።" *ዘጸ 32፡12።*

4. የሶርያም ንጉሥ አዛሄል በኢዮአካዝ ዘመን ሁሉ እስራኤልን ባስጨነቀ ጊዜ "እግዚአብሔር ግን ራራላቸው፥ ማራቸውም፥ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ስላደረገውም ቃል ኪዳን እነርሱን ተመለከተ ሊያጠፋቸውም አልወደደም፥ ፊጽሞም ከፊቱ አልጣላቸውም።" *ካል ነገ 13፡23።*

5. አሮንና ማርያም ሙሴን ባሙት ጊዜ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ስለምንናገረው የሚቆጣ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። "እርሱም፦ ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፥ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፥ በምሳሌ አይደለም የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም? አለ።" *ዘኍ 12፡6-8።*

6. ሌላው እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ የሰጠውን ክብር የሚገልጥልን "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።" *ሉቃ 10፡16*፣ "የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።" *ዮሐ 12፡26።*

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።